# ፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ (ሁለት)

ዮናስ 4/4/12

**ቦአዚዝ፣ መጅሊስ፣ መምህራን - - - የከሰሩ ፖለቲከኞች ጩኸት**

ብዙም ባልራቀ አንድ ወቅት የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ በዚሁ ጋዜጣ ላይ ሃገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ይዳሰሱበታል በሚለው አንድ በሉ አምድ ስር የአረቡን አለም አብዮት በተከታታይ ሲያስተጋባና ሲቀሰቅስበት ከቆየ በኋላ የዓመጹ ጥሪ ሰለባ እንዲሆኑ የተመኛቸው ወጣቶች ምላሽ ቢነፍጉት ግራገባው መሰል |አንተማ ምን ታደርግ ፈሪዋ እናትህ ነች´ ብሎ በመጻፍ ጉድ አሰማን።

"ፈሪዋ እናትህ ነች!" ያለበትን ምክንያት ሲያብራራም አመጹና አብዮቱ መላውን አረብ እያጥለቀለቀ ኢትዮጵያዊው ወጣት ዝም ያለው እናቱ ስላስፈራራችው እንጂ ኑሮ ተመችቶት አይደለም። እናቱ ያስፈራራችበት ምክንያት ደግሞ አንጀቷ ስለማይችል፣ ሆድ ስለሚብሳትና ሌላም ሌላም ምክንያት ደረደረ። እኔ ግን ታዘብኩት። ለምን ቢባል የአድዋን በአል ተንተርሶ ደግሞ ጣይቱን አብነት በማድረግ የእናትን ደፋርነት ያወሳበትን ጽሁፍ በማንበቤ። ዳሩ አላማው የዜሮ ድምር ፖለቲካ አስተሳሰብ ነውና ዛሬ የተናገረውን ነገ ቢክድና ቢዘነጋ አይገርምም።

በተለይ የ2004 ዓ.ም ዋዜማ በሆነችው ጳጉሜን ፍትህና ዓምደኞቿ መስከረም አመጹ ከወረቀት ወደተግባር መሸጋገር ያለበት ወሳኝ ወቅት ይሆናል ሲሉ ነጋሪት ጎሰሙ፣ መለከትም ነፉ። በዚህ ወቅት በተለይ ፍትህና ዓምደኞቹ ነጋሪት ቢመቱም የሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ ባልደረቦቻቸው ከፍኖተነፃነት እስከ አዲስ አድማስ ልፈፋውን ተቀባብለውት ነበር። ለአዲስ ዓመት እንደተለቀቀ የአዲስ ዘፈን ማስታወቂያና የዘመን መለወጫ ብስራት በሚመስል ቃና የአመጽና የሁከት ጥሪውን ለብቻቸው አዜሙት፡፡ ደጋሽ ራሳቸው፤ ተጋባዥም አድናቂም ራሳቸው ብቻ ሁነው አረፉት እንጂ፡፡

የአረቡ አለም አመጽና አብዮት የራሱ ምክንያት ስለነበረውና በኢትዮጵያ ተመሳሳይ አመጽ ሊከሰት የሚችልበት ምንም አይነት መሰረታዊ  መነሻ የሌለ በመሆኑ "የአብዮቱ" ጥሪ ሰሚ አጣ። ከዛም "ፈሪዋ እናትህ ነች" ያለው ተመስገን ደሳለኝ |የናትህ ፍራቻ ይወገድ ዘንድ ስለ ቦአዚዝ ንገራት፣ ስለግብጽ ወጣቶች ተርክላት፤ የምትነግራት ካጣህ ናና ከኔ ቢሮ የአብዮቱን ሲዲ ውሰድና አሳያት´ ብሎ    እርፍ አለው። ለካስ የተመስገን ቢሮ ሲዲም ይሸጥበታል፤ወይም ይከፋፈልበታልና!እግረ መንገዱን ማስታወቂያ ሰራብን አይደል? ለመሆኑ የንግድ ፈቃድ አውጥቶ እየሰራ ነው አይደለም የሚለው አጀንዳችን ስላልሆነ የሚመለከተው አካል ይጠይቀው ብለን ለጊዜው እንለፍ፡፡

የተመስገን ሲዲ የያዘው የአብዮት ይሁን የሁከት፤የአመጽ ወይም የግርግር....፤(ለነገሩ ሁሉም ያው ነው ለሱ) ጥሪ የሚያውቀውና የሚያውቁት እሱና አጫፋሪዎቹ ናቸው፡፡ እኔ በበኩሌ ተመስገን የሚለውን ሲዲ ገበያ ላይ አግኝቼ በመግዛት የማዬት ዕድል ስላላገኘሁ ራሱ በተናገረው ላይ ብቻ ተመስርቼ አስተያዬት እየሰጠሁ እንደሆነ ልብ በሉልኝ፡፡ የሆነስ ሆነና እንዴት ነው ነገሩ አብዮትና ዓመጽ ከልብ ከመነጨ ብሶት ይወለዳል እንጂ በሲዲ በሚታይ ምናባዊ ልብ ወለድ ፊልም በደመነፍስ ይቀሰቀስ ይሆን? እዚህ ጋር ነው እንግዲህ የፍትህና የአምደኞቹ አይን ያወጣ ስህተትና ውንብድና።

ያሰቡት እንደማይሆን ቀድሞውኑ የሚያውቁት እነፍትህና አምደኞቹ አብዮት በፊልም ለማስነሳት መቋመጣቸው ግን ሲሻቸው ጀግና ሲያሻቸው ደግሞ ፈሪ የሚሉትን ህዝብ መናቅ መሆኑን መረዳት ነበረባቸው። ከዚህ በላይ ሕዝብን ማዋረድ ሊኖር አይችልም፡፡

ተወደደም ተጠላ ምንም እንኳ መላው ወጣት በስርዓቱ ተጠቃሚ ባይሆንም የሚበዙቱ ግን ፍትህና ዓምደኞቹ በሚያጥላሉትና በሚያንቋሽሹት ጥቃቅን እና አነስተኛ ተደራጅተው ህይወታቸውን እየለወጡ ነው። ከ100 ሺህ በላይ የሚሆኑት ደግሞ በየዩኒቨርስቲው የትምህርት ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። ከዚህ ቁጥር የሚልቁትም በቴክኒክና ሙያ ትምህርት እያገኙ ስራ ፈጣሪ መሆናቸው እርግጥ እየሆነ መጥቷል።

ሁሉም በየዘርፉ የልማቱ ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን የልማቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ እየሆነ መምጣቱ ዕውን ሆኗል። ግን እዚህም እዚያም ስህተትና የተጎዳ አይጠፋም ማለት ባይቻልም ለአመጽና ለአብዮት የሚዳርግ ምንም ተጨባጭ ምክንያት ግን ፈጽሞ የለም። አብዮት ደግሞ ከምናባዊ የፊልም ድርሰት አይወለድም፤ ባህሪው አይደለማ፡፡ አብዮት ከነባራዊ ሁኔታ የሚወለድ የኢ-ዴሞክራሲያዊ ስርአትና የዚህ ውጤት የሆነው የብሶት ልጅ ነው።

ፍትህና ዓምደኞቹም ይህንኑ በመረዳት ይመስላል ተስፋ ቆርጠው ከተቀመጡ ጥቂት ወራት በኋላ የነቡአዚዝን ጉዳይ የሚያነሱበት አጋጣሚ የተፈጠረላቸው ስለመሰላቸው ዛሬ ደግሞ በ"ጭር ሲል አልወድም" ውዝዋዜአቸው ከወጣቱ ነቅለው ወደ መምህራን ዞረዋል። መጅሊሱና አወልያም፣ ዋልድባና ዙቃላም ለማላዘን እንደጥሩ አጋጣሚ ጠቅሟቸዋል። ስለዚህም የከሰረውን የፖለቲካ ጩኸት የተባበሩ ጩኸቶች ሲል ቡአዚዝን፤መጅሊሱንና መምህራንን ተመስገን ደሳለኝ ከአንድ ቤተሰብ መደባቸውና በአንድ ከረጢት ውስጥ ከተታቸው። የኔሰው ገብሬ የተባለውን (የአይምሮ ህመምተኛ እንደነበረ በቅርብ ከሚያውቁት ሰዎች ተነግሯል) ደግሞ ኢትዮጵያውያኑን መምህራንና ቡአዚዝን በዘር አገናኝቶበታል ጉደኛው ተመስገን ደሳለኝ።

የቡአዚዝን ጉዳይ የሚተርክልን ተመስገን ደሣለኝ ለቡአዚዝ ነዳጅ ያቀበለ ወይ የገዛለት ወይ ደግሞ እንደጠባቂ መላክ በመንፈስ የተከተለው ይመስላል። የቡአዚዝን ፀሎት ጭምር ሊያወሳን ሞክሯልና። አላህ ጀነትን ያወርሰው ዘንድ ያሰማውን ፀሎት። “ለማያውቅሽ ታጠኝ” እንዲሉ አባቶች፤ ተመስገን ይህን ጉዝጎዛና "አንጀት መብላት" እዛው ብትተወው ጥሩ ነው ስል እመክርሃለሁ። በማያውቁት ነገርና በማይገናኙ ጉዳዮች ላይ ገብቶ መዳከር ትረፉ ከንቱ ድካም ነውና ንፁህ ሕሊና ካለህ እዚሁ አጠገብህ ያለውን ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታውን የሚረዳ ሕሊና ሊኖርህ ይገባል፡፡ አሁን አሁንማ ነገርህ ሁሉ “ዝሆን ይኸውና ቢሉት ዱካውን ካላየሁ አላምንም!“ ያለውን ጅላጅል ሰው ያስታውሰኝ ጀምሯል፡፡

ለምን? ብትል ወጣቱ ቀደም ብዬ በነገርኩህ ሁኔታ ላይ ነው የሚገኘው። እራሱን ለማቃጠል አይደለም እንቅፋት እንዲነካው የማይፈልግበት በስራ የተወጠረበት ዘመን ላይ ነው አሁን። መጅሊሱንም ቢሆን ብተተወው ጥሩ ነው። እውነታውን አብዛኛው የሙስሊሙ ማህበረሰብ ስለሚረዳው የአወልያው ስብሰባና የጥቂቶች ሰርጎገብ ጥያቄ  ተላላኪው ሃይል ለሽብርተኝነት የተመቸ ሁኔታ ይፈጠርለት ዘንድ  ያመቻቸው መሆኑን በትክክል ተገንዝበው ጉዳዩ በሰላማዊ ውይይትና በመተማመን መንፈስ ጉዳዩ እልባት እያገኘ መጥቷል። ጥያቄው የጀመረው ደግሞ ከሰሞኑ በአወልያውና በመጅሊሱ መካከል ከተፈጠረው አለመግባባት እንዳይመስልህ።

የነዚህ አሁን በአወልያው ስብሰባ ውስጥ የገቡትን ሰርጎ ገቦች የመጀመሪያ ሙከራ የተቃጣው በትምህርት ተቋማት አካባቢ ነበር። ስለሆነም የትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት እና ህገመንግስቱን በመንተራስ የትምህርት ተቋማት ከማንኛውም የእምነት ቦታነት ወይም ማምለኪያነት የፀዱ የሚሆኑበትን መመሪያ ሲያወጣ የተጀመረ ጠብ አጫሪነት ነው አንተ የምትለው የመጂሊሱ ጉዳይ።

መመሪያው ምን ነበረ? ካልከኝ አስታውስሃለሁ። አንተም ስለጉዳዩ አብረውህ ለሚያላዝኑት ዓምደኞችህና የፓርቲ አጋሮችህ ትነግራቸዋለህ። ነውጠኛ ለሆኑት ዲያስፖራ አለቆችህና አዛዦችህ ኢ.ሜይል ታረግላቸዋለህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

|የከፍተኛ ትምህርት፣ ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትና ትምህርት ቤቶች የአምልኮ፣ የአለባበስና የምግብ ስርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 003/2003´ ይላል የመመሪያው ሙሉ ርዕስ።

ሶስት ምክንያቶችን በመጥቀስ መመሪያው ያስፈለገበትን መስፈሪያ ከመግቢያው ያስቀምጥልናል።

ትምህርት ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከትና ከባህላዊ ተፅእኖዎች ነፃ መሆን እንዳለበት ህገመንግስቱ መደንገጉን፤ ትምህርትና የትምህርት ተቋማት ከሃይማኖት ወገንተኝነት ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ ስለሚያስፈልግ፤ ተቋማቱን ሰላማዊ የመማር ማስተማሪያ መድረክ ማድረግ

ስለሚገባና በሃይማኖት ሽፋን በሚደረጉ ህገ ወጥ ድርጊቶች ሰለባ እንዳይሆኑ መከላከል ስለሚገባ። የሚሉት ናቸው የመመሪያው አስፈላጊነትን የተመለከቱት ነጥቦች። ይህን መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ደግሞ ከአንድ መንግስት የሚጠበቅና ሃላፊነትን መወጣት ነው። መንግስት መመሪያውን በማውጣት በቀጥታ ተግባራዊ እንዳላደረገውም ላስታውስህ እፈልጋለሁ።

መመሪያው እንደአስፈላጊነቱ ህገ መንግስቱን መሰረት አድርጎ በየአመቱ የሚሻሻልበትን ዕድል አካቶ የወጣ ሲሆን የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ማህበረሰቦችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላቶች ተወያይተውበት ከተስማሙበት በኋላ የፀደቀ ነው።

ይህ መመሪያ ዕድላቸውን የዘጋባቸውና በሃይማኖት ሽፋን ኪራይ ለመሰብሰብ የታጠቁ አንተን መሰል ፖለቲከኞች ወይም አምደኞች ታዲያ ጉዳዩን ወደመጅሊሱ አዞሩና በአወሊያው ኮሚቴ በኩል ብቅ አሉ።

አንተና አምደኞችህ በአንዱ ሲሏችሁ በሌላው ፤የአረቡ አለም አብዮት ሳይሳካ ወደሊዝ ስርዓቱ ፤ይህም ሲከሽፍ ወደግብር አሰባሰብ ስርዓቱ፤ ይህም መንገድ የተዘጋ ሲመስላችሁ ወደ ጋምቤላ የእርሻ ኢንቨስትመንት ስትቀያየሱ ከረማችሁ። ይህ ሁሉ ሲነቃባችሁ ደግሞ ሰሞኑን ቦአዚዝ፣ መጅሊስ መምህራን ብላችሁ እንደመጣችሁት በትምህርት ተቋማቱ የዘረጉት መረብ የተበጣጠሰባቸው ፀረ ሃይማኖት ቡድኖች መጅሊሱንና አወልያውን መጋለቢያ ሜዳ ሊያደርጉት ቢሞክሩ አይገርመንም። ለምን ?ቢባል በአባት አንድ ናችሁና። ዋናው ነገር ግን መመሪያው የነዚህን ኪራይ ሰብሳቢዎች መረብ ከመበጣጠሱም በላይ ምቹ የመማር ማስተማርን ሂደት መፍጠሩ ነው።

ከምንም በላይ ደግሞ ሰላምና ፀጥታን አስፍሯል። የተባበሩት ጨኽቶችን ያስነበብከን ተመስገንም ሆንክ ሰላማዊ ትግል አብቅቶለታል የሚለን ዓምደኛህ ከህዝቡ አንጀት ውስጥ ለመግባት ያስችለን ይሆናልና እንሞክረው በሚል የከሰረ እሳቤ፤ የተለያዩ ሃገሮችን ልምድና የጥናት ወረቀቶችን ቀነጫጭቦና ቆነጣጥሮ በሚስማማችሁ መልኩ ቃላቶችን በመገጣጠም መጥቀስን እንደ አንድ ዘዴ ትጠቀማላችሁ። ይህ ደግሞ አረፍ ዘዴ ነው። "ከአረፍ ደግሞ ይኮረጃል" እንዲሉ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ የትምህርት ሚኒስቴርን መመሪያ ተገቢነት ተጨባጭ ለማድረግ እኔም የሃገራትን ተሞክሮና ጥናት ብጠቀምስ፦

እ.ኤ.አ. 2004 ፈረንሳይ ውስጥ የትምህርት ተቋማትንና የሀይማኖት ጽንፈኝነትን ዝምድና በገሃድ የሚያሳየኝ አንድ ታሪክ ተፈጽሟል፡፡ መጋቢት 15,2004 በቀረበላቸው አስቸኳይ ሰነድ ላይ ፊርማቸውን ሲያኖሩ ፕሬዝዳንቱ ላላቅማሙም ነበር፡፡ ከመስከረም 4 ጀምሮ በመላው የፈረንሳይ የመንግስት ት/ቤቶች ውስጥ የሚተገበርን አዲስ ሕግ ይዟል- ሰነዱ፡፡ እንዲህ የሚል አንኳር ይዘት አለው፡-

‹‹ከመስከረም 4,2004 ጀምሮ በፈረንሳይ መንግስት በሚተዳደሩ ት/ቤቶች ውስጥ ‹‹ሀይማታዊ ትርጓሜ (conspicuous signs of religion) ያላቸውን›› አልባሳትና ቁሳቁስ መጠቀም ተከልክሏል››

ይሄንን ውሳኔ የሺራክ መንግስት ከመሬት ተነስቶ በአንድ ጀምበር  አላስተላለፈም፡፡ ፕሬዝዳንቱ ራሱ ባቋቋሙት 20 አባላት ባሉት ኮሚቴ ሰፊ ጥናት ከተካሄደ በኋላ ነው፡፡ በወቅቱ አነጋጋሪ የሆነው ይህ ህግ በመላዋ ፈረንሳይ ሥራ ላይ የዋለው በህጉ መሰረት የእስልምና ተከታይ ሴቶች የሚለብሱት ሂጃብ፣ የአይሁዳውያኑ ኪፓ፣ የሰኪዎቹ (ህንዶች) ጥምጣም፣ ትልልቅ መስቀሎች እና ሌሎች ሀይማኖታዊ ምልክቶች በሙሉ በትምህርት ተቋማት እንዳይለበሱ ታገደ፡፡

መመሪያው አፈጻጸም ላይ ጠንካራ እንዲሆን በማሰብም ለየትምህርት ቤቶቹ ሀላፊዎች ልዩ ልዩ የአስገዳጅነት ሥልጣኖችን በመስጠት እንዲተገበር ተደረገ፡፡

የእኔ ትኩረት የፈረንሳይ አልባሳቱን በደፈናው የመከላከሏ ዜና አይደለም፡፡ ከጀርባው የተሰጡት ከሀገሮቹ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ምክንያቶች እንጂ፡፡ የመጀመሪያውና ዋነኛው የትምህርት ተቋማትና ሃይማኖትን ለያይቶ ማየቱ የጠነከረ መሰረት እንዲኖረው በማሰብ ነው፡፡ እነ ናፖሊዎን ቦናፓርቴ ለቤተ እምነቶች ሰጥተውት የነበረውን ነጻነት ይነፍጋል፡፡ ከሁሉ በላይ ግን በወቅቱ ህጉን በማውጣት አስፈላጊነት ዙሪያ የፈረንሳይ መንግስት ይሰጣቸው ከነበሩ ምክንያቶች ውስጥ ይኼኛው ከእኛ ሀገር እውነት ጋር ይጣጣማል፡፡

እነዚህ ሀይማኖታዊ መገለጫዎች ላይ እንዲህ አይነት ህግ ካልወጣ እየዳበረ ያለውን የፈረንሳይ ብዝሃነት /plurality/ አደጋ ላይ ይጥሉታል፡፡ የሀይማኖትም ሆነ የባህል ልዩነቶቹን አቻችሎ በሚኖረው የፈረንሳይ ህዝብ ላይ እንደዚህ አይነት ሀይማኖታዊ መገለጫዎች በርካታ መዘዝ ይዘው ይመጣሉ››፡፡ የቁጣና የመከፋፈል (coercion and divisiveness) ሚናቸው የሰላ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ እያደገ ለመጣው የሽብርተኝነትና የፅንፈኝነት አካሄድም ተጋላጭ ይሆናሉ የሚል ነበር፡፡

ውሳኔው በወቅቱ የበርካታ ውዝግቦች መነሻ ቢሆንም ከተቃወሙት አብዛኛዎቹ ግን የሂጃብን መከልከል በዋናነት በማንሳት ክስተቱን በቀጥታ ከእስልምና ሀይማኖት ጋር አያይዘውታል፡፡ ህጉ ዘላቂነት እንዲኖረውም የእስልምና አክራሪ ቡድኖች የሀገሪቱን ሁለት ጋዜጠኞች በማፈን (የኢራቅ ኢስላማዊ ጦር በዋናነት ይጠቀሳል) ታግለዋል፡፡ በወቅቱ 11% ያህል ሙስሊሞች አክራሪ ቡድኖች አንገት እስኪደፉ ድረስ አብዛኛው የሀገሪቱ ሙስሊም ዜጋ ውሳኔውን በጸጋ ተቀብሎ ኑሮውን ቀጠለ፡፡ ይህ እውነትም ስለ አለምአቀፋዊ የሀይማኖት አክራሪነት ገጽታ የራሱን ሚስጢር ጥሎ አለፈ፡፡ የዜጎችን ሰላም ይጠብቃል፣ ሕብራዊነታችንን ያጠናክራል፣ የሕዝቤን ባህልና ወግ ያከብራል ያለችውን ሕግም ፈረንሳይ በደስታ (ከነተቃውሞው) እነሆ ቀጠለችበት፡፡ የመንግስት፣ የሀገር ከሀይማኖት ገለልተኛነትም ከፍ ብሎ ታየ፡፡

ተጨማሪ እውነት ለተመስገን እና ለአምደኞቹ ፡-ታላቁን የኢስታንቡል ዩኒቨርሲቲ የ31 አመቷ ተማሪው ፍርድ ቤት ገተረችው፡፡ ሰኔ 2004 ውስጥ የዋለው የአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት የ31 አመቷን የኢስታንቡል ዩኒቨርሲቲ የህክምና ተማሪ ላይላ ሳሂን ያቀረበችውን ክስ በጥሞና እያዳመጠ ነው፡፡

የክሱ ይዘት እንደሚያስረዳው፡-
‹‹በ1998 በዩኒቨርሲቲው የ5ተኛ ዓመት ተማሪ የነበረችው ላይላ ሂጃብ በመልበሷ በተቋሙ ውስጥ የሀይማኖት ልብሶች እንዳይለበሱ የሚደነግገውን አዲስ ሕግ ተላልፈሻል ተብላ ፈተና እንዳትቀመጥ መከልከሏን ያስረዳል…››

ይህ ብቻም አይደለም አዲሱን ሕግ በመቃወም ዩኒቨርሲቲው ሳይፈቅድ የአመጽ ስብሰባዎች ላይ በመሳተፏ ቅጣት እንደተላለፈባት ፤ ይህ ደግሞ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንደሆነ አለምአቀፋዊ ህጎችን በመጥቀስ ለአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት ማቅረቧን ያስረዳል፡፡ ሌሎች የሕግ አንቀጾችን በተለይም ቱርክ የተቀበለችውን አለምአቀፋዊ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ማግለል እና አድልኦ እንደተፈጸመባት፣ ህጋዊ መብቷ መገደቡን፣ የመማር መብቷ መነፈጉን፣ የሀይማኖት መብቷ መጣሱን ወዘተ.. በማስረጃ በማቅረብ ከሳለች፡፡

ከአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 18 ጀምሮ እስከ አውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 8፣ 9፣ እና 10 ድረስ በመጥቀስ ነው ላይላ ክሷን አደራጅታ ያቀረበችው፡፡ በወቅቱ ደጋፊዎቿ የነበሩ ወገኖች በሙሉ ፍትህ ወደ ላይላ እንዳጋደለች አምነው ነበር፡፡

ክሱን በጥልቀት ያዳመጠው አውሮፓ ሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት ግን አንዳቸውንም የላይላን ክሶች ሳይቀበላቸው ቀረ፡፡ የመጀመሪያ ምክንያቱም የቱርክ መንግስት ሕገ መንግስታዊ መብቶች ከማክበር የተመዘዘ ሆነ፡፡ የሰፊው ህዝብ መሪ የሆነውና (የግል እንጂ የቡድን ሀይማኖት) የሌለው መንግስት (secular republic) ለሰዎች የማይመቹ ሃይማኖታዊ መገለጫዎችን፣ አለባበሶችን የመቆጣጠር፣ የማገድ ሕገመንግስታዊ ስልጣን እንደተሰጠው፤ ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚወጡ ደንቦችና ሕጎችን የማስፈጸም አቅም እንዳለውም ፍርዱ አብራራ፡፡ በ1998 የኢስታንቡል ዩኒቨርሲቲ ሀይማኖትና የትምህርት ተቋማትን ለይቶ ለማየት እንዲያስችሉት የተገበራቸውን ደንቦች ከግምት ያስገባ ማንኛውም ቅን ዜጋ የላይላ አይነት ክስ ይዞ ፍርድ ቤት አይቆምም የሚል ድምዳሜውን ሰጠ ፍርድ ቤቱ፡፡

ፍርድ ቤቱ ለቱርክ መንግስት የፈረደበትን ምክንያት ሲያብራራም ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶችን አስቀመጠ፡፡ የመጀመሪያው ከዘመናዊው የቱርክ አባት ሙስጠፋ ከማል አታ ቱርክ ዘመነ መንግስት 1923 ጀምሮ የቱርክ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የተገነባው ከሀይማኖት ነጻ በሆነ መሰረት ላይ በመሆኑ

ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሀገሪቱን ባህላዊና ሀይማኖታዊ ብዙሃነት ለማስጠበቅ ሁነኛ መንገድ ነው፡፡ ለዚህ ሁነኛ ማሳያ ደግሞ ዘመናዊነትን የሚያፋጥን ነጻ የትምህርት ተቋም መፈጠሩ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት በሕግ ፊት ሁሉም ዜጋ እኩል መሆኑ መረጋገጥ ስላለበት ነው፡፡ የሌሎች ዜጎች መብቶች በአንደኛው ዜጋ ድርጊት መገሰስ የለባቸውም፡፡ ሰዎች ሃይማኖታቸውን የሚገልፁ አልባሳት በተጠቀሙ ልክ ለተመልካቹ ትርጉም ያለው መልእክት እያስተላለፉ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል፡፡ ሶስተኛው ምክንያት በቀጥታ የተያያዘው የሃይማኖትን ግለሰባዊ ትርጓሜ ከማጉላትና ከፖለቲካ ለይቶ ከማየት ነው፡፡ ስለዚህ ብዙዎችን ያስገረመው ውሳኔ አሸናፊነቱን ለቱርክ ሰጣትና በ45 ግዛቶቹ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሕጉን ተገበረችው፡፡ ከሳሿ ላይላም አውስትሪያ ሄዳ ትምህርቷን አጠናቀቀች፡፡

እንዲህ አይነት ምሳሌዎችን በመላው አውሮፓና አሜሪካ እየተዟዟርን መሰብሰብ እንችላለን፡፡ በተለይ ከመስከረም 11 ጥቃት በኋላ የሀገር ደህንነትን በመጀመሪያ ረድፍ በማስቀመጥ ሀገራት በዜጎች ሀይማኖታዊ እንቅስቃሴ ዙሪያ ጠንካራ ክትትል ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ክትትሎች ሁሌም ማለት ይቻላል በየአይነቱ ተቃውሞ ይዘጋጅላቸዋል፡፡ ሀገራቱ ግን ተቃውሞዎቹን ፈርተው ስራቸውን ከመስራት አይቆጠቡም፡፡ ለፍተው ለትምህርት ያደረሷቸውን ዜጎቻቸውን በአክራሪነት አስተሳሰብ እንዳይነጠቁ በመስጋት የትምህርት ተቋሞቻቸውን በአይነ ቁራኛ ይጠብቃሉ፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቻቸውና የተለያዩ የትምህርት ተቋሞቻቸው ላይ ከፍተኛ ስራ ይሰራሉ፡፡የኛም መንግስት ለዜጎች ደህንነት ሲል ያደረገው ይህንኑ ነው። ስለሆነም እልሃለሁ ተመስገን "ሊበሏት ያሰቧትን..." እንዲሉ ያንተንና የመሰሎችህን ጩኸት በተባበሩት ስም በመጅሊሱና በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ባታላክክ ጥሩ ነው። ወደ መምህራኑ ሰሞንኛ አጀንዳ ልውሰድህ ።አንተና አምደኞችህ ጩኸት ብትሉትም መምህራኑ በማህበራቸው አማካይነት መጀመሪያ ያቀረቡት የመብት ጥያቄ ነው፤ቆሞ የነበረው የደሞዝ ደረጃ እርከን ማደግ። ጥያቄአቸው በቀረበበት አግባብ ምላሽ እንደተሰጠው ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠ መግለጫን አዳምጫለሁ፡፡ ለእርከን ጥያቄው ምላሽ የሰጠው መንግስት በአንዳንድ ወገኖች የደሞዝ ጭማሪ እንደሆነ ሆኖ ተስተጋባ። ከዛም አንዳንድ መምህራን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ክብራችን ተነክቷል ሲሉ ድምጽ አሰሙ።

ክብራቸውን ያላወቁ መምህራን ያልኩበትን ምክንያት ልንገርህ ።አንተ ደግሞ ለአምደኞችህ ትነግራቸዋለህ። ከዩኒቨርስቲ በመጀመሪያ ዲግሪ አዲስ የተመረቀ የመንግስት ሰራተኛ የትም ይምደብ የትም በፕሳ(ፕሮፌሽናል ሳይንስ)መነሻ ደሞዙ 1499 ብር ነው። ጀማሪ መምህር ደግሞ 1571 ብር ነበር። ሰሞኑን በተደረገው ማሻሻያ ደግሞ 1644 ብር ሆኗል። እኔ በቅርብ በማውቀው በአዲስ አበባ ሁኔታ 300 ብር የቤት አበልም ይከፈላል።

ከብዙ በጥቂቱ እኔ እስከገባኝ ድረስና ሌላውም ቅን ልቦና ያለው እንደሚረዳው በቃ እውነታው ይህ ነው፡፡ ከዚህ ጋር የተያያዘ ምንም አይነት ቅሬታ እንኳ ቢኖር በቀጣይ በውይይት፤ በመግባባትና

በመተማመን የማይፈታበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ ይህ ደግሞ ዴሞክራሲያዊና ብስለት ያለው የሰለጠነ አካሄድ ነው፡፡ ተመስገን አንተና ተከታዮችህ ያልገባችሁ ነገር አለያም ሆን ብላችሁ ለማደናቆር እንደምትሞክሩት (ይህ በትክክል ይገልጻችኋል ብዬ አስባለሁ) ሳይሆን ሰዎቹ እኮ መምህራን ወይም መሁራን ናቸው። እናንተ ሌላ የውኸ'ንብር አጀንዳ ድንገት ፈነዳልን ብላችሁ ጮቤ በመርገጥ እንደፈለጋችሁ የትም በምትቀዱት ቦይ ገብተው የሚነዱ አይደሉም፡፡ እናንተ ግን በርእሰ አንቀፃችሁ ጭምር  የደገፉችኋቸው  በማስመሰል ልታስጮኹ ብትሞክሩም መምህራን ግን የናንተ የተንኮል ሰለባ እንደማይሆኑ ልትረዱት ይገባል። ፊዚክሱን ከሂሳብ፣ ታሪክን ከቅኔ አገለባብጦ ለሚተነትን መምህር ያንተ እና የአምደኞችህ ውስጠ መርዝ ቅስቀሳ አጀንዳው ስላልሆነ ያው እንደተለመደው ደግሞ ሌላ ሰሞነኛ የጩኸት ምናባዊ የፈጠራ ፊልም ለመስራት እራስህን አድክም፤እኔም እንደገና በምታነሳው……. መመለሴ የሚቀር አይመስለኝም።

ስለሆነም ፍትህና አምደኞቹ ከኢጋር ፓርቲያችሁ ፍኖተ  ነጻነትና ኢሳት ጋር የተባበሩ ጩኸቶችን ማሰማታችሁን ትቀጠሉ እንደሆነ እንጂ ቦአዚዝ መጅሊስና መምህራን የተባበሩ ጩኸቶች አይደሉም፤አይገናኙማ። እቀጥላለሁ ፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ  ሶስት።